# መሪዎቻችንን ታዘብናቸው

**ክፍል ሁለት**

**ተፈሪ መኮንን**

**05-23-18**

ይህን ሐተታ ያመጣሁት፤ ከመነሻዬ በጠቀስኩት የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለስልጣን ባዘጋጀው የውይይት መድረክ የተነሱ አንዳንድ ጉዳዮችን መነሻ አድርጌ የተወሰኑ አስተያየቶችን ለመስጠት ነው፡፡ የኢትዮጵያ የብሮድካት አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ የታወጀው በ1991 ዓ.ም ነበር፡፡ የመስሪያ ቤቱ አሰራር እና አዋጅ ዘመኑን የዋጀ አይደለም፡፡ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ በታወጀ ጊዜ የያዛቸው አንዳንድ ድንጋጌዎች ኋላ ቀር ነበሩ፡፡ በመስኩ ያለው ለውጥ ፈጣን በመሆኑ አሁን ይበልጥ ኋላ ቀር መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በዚህ ዘርፍ ያሉ ፖሊሲዎች (ካሉ) እንደገና መፈተሽ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ አዋጅ ባወጣበት ጊዜ የነበሩት ሁኔታዎች ዛሬ ፍጹም ተቀይረዋል፡፡ በአዋጁ ላይ በ1999 ዓ.ም የተወሰኑ መናኛ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

አሁን በሥራ ላይ ያለው የብሮድካት አዋጅ፤ የአየር ሞገድ ውሱን ሐብት መሆኑን መነሻ በማድርግ የታወጀ አዋጅ ነው፡፡ ሆኖም የዲጂታል ቴክኖሎጂ መፈጠር የአየር ሞገድ ውሱን ሐብት መሆኑን አስቀርቶታል፡፡ ስለዚህ የብሮድካስት አዋጁ ለመጀመሪያ ጊዜ በመወጣ ጊዜ ‹‹የአየር ሞገድ ውሱን የህዝብ ሐብት ነው›› በሚል የያዘው መነሻ ዘመኑን ያልዋጀ መነሻ በመሆኑ ይተች ነበር፡፡ በወቅቱ፤ አዋጁ የቴክኖሎጂ ጥበብ አልፎት የሄደ ገደብን ያስቀምጣል የሚል ክርክርም ይነሳ ነበር፡፡ ዛሬ በቀላሉ ‹‹የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን አገልግሎት›› ለመስጠት ይቻላል፡፡ በአንድ በኩል፤ የማሰራጫ ቁሳቁሶቹ እንደ ሻንጣ በቀላሉ ሊያዙ የሚችሉ እና ከማንኛውም ሰው እጅ በቀላሉ ሊገቡ የሚችሉ ነገሮች ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል፤ አገልግሎቱ ከኢንተርኔት ጋር ተያይዞ ይበልጥ ቀላል ሆኗል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሐገራችን የብሮድካስት አዋጅ ‹‹የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሐይማኖት ድርጅቶች የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸውም›› የሚ ክልከላ አስቀምጧል፡፡ ይህን አዋጅ ተፈጻሚ ማድረጉ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ተፈጻሚ ሊደረግ የማይችል አዋጅ ማውጣት ደግሞ ትርጉም የለሽ ይሆናል፡፡ አዲሱ የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ ለአጠቃቀም ቀላል እና የማይገደብ የተደራሽነት ዕድል የሚከፍት በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ

የብሮድካስት ባለስልጣን የአገልግሎት ፈቃድ የሰጣቸው የቴሌቭዥን እና የሬድዮ ጣቢያዎች ወደ አዲሱ ምህዳር እየተሰደዱ ነው፡፡ ፋናን ወይም ኢቢሲን በኢንተርኔት ለመከታተል የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ ሁኔታ በአዋጁ የተጠቀሰውን ‹‹ሐገር አቀፍ ስርጭት፣ የክልል ስርጭት፣ የማዘጋጃ ቤት እና የማህበረሰብ›› በሚል የሚሰጠውን የአገልግሎት ፈቃድ ትርጉም የለሽ ያደርገዋል፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያለው የብሮድካት አገልግሎት ከሁኔታዎች ጋር መጣጣም የሚገባቸው በርካታ ድንጋጌዎችን የያዘ ነው፡፡

አሁን የታየው አዲስ የቴክኖሎጂ ክስተት የብሮድካስት ባለስልጣን አሰራርን ብቻ ሣይሆን፤ ራሱ ‹‹መንግስት›› የተሰኘውን ተቋም ጊዜ ያለፈበት እንዲመስል እያደረጉት ነው፡፡ ዛሬ ለወትሮው የሚታወቀው የመንግስት የቁጥጥር አቅም በቦታው የለም፡፡ አዲሱ ምህዳር አዳዲስ ሽፍቶችን ፈጥሯል፡፡ የዘንድሮ ‹‹ሽፍታ›› ሶማ፣ ተከዜ ወይም አባይ በረሃ መሄድ አያስፈልገውም፡፡ አውሮፓ፣ አሜሪካ እና እዚሁ አዲስ አበባ ሆኖ መሸፈት ይቻላል፡፡ ‹‹ጉድ በል ጎንደር›› ማለት አሁን ነው፡፡

የሐገራችን የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሰጪ እና ተቆጣጣሪ የሆነው የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን፤ ማድረግ የሚችለው እና የማይችለውን ለይቶ፤ ራሱን ከአዲሱ ሁኔታ ጋር ለማስማማት እንደገና ጥናት ማድረግ አለበት፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ የኢትዮጵያ የብሮድካት ባለስልጣን ፈቃድ የሰጣቸውን የመንግስት፣ የንግድ እና የማህበረሰብ የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ጣቢያዎችን ለመቆጣጠር የማይችል ደካማ ተቋም መሆኑን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሆኑት ነገሮች አይተናል፡፡

ሐገር ስትቃጠል ዝም ብሎ ሲመለከት የነበረው ባለሥልጣን አንዳንድ የመንግስት የመገናኛ ብዙሃንን ‹‹ህገ መንግስቱ ሲቃጠል እና ሐገር ከፊቱ ሲፈርስ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር›› ብሎ ሲከስስ ሰምተናል፡፡ እርሱ ዝም ብሎ፤ ሌሎችን በዝምታ ይከሳል፡፡ ብሮድካስት ባለስልጣን ሊያደረግ የሚገባውን ነገር ባለማድረግ፤ ሌሎች ደግሞ ማድረግ የማይገባቸውን ነገር በማድረግ፤ ሁለቱም ህገ መንግስቱን ሲጥሱት እና ሲንዱት ከርመዋል፡፡ ቀልደኛ ነው፤ ‹‹ከበትሩ ካሮቱ ይለናል፡፡›› ሐገር እየፈረሰ በካሮት እና በበትር መካከል ምርጫ ይዟል፡፡

ብዙ የመንግስት ሚዲያዎች ህዝብን በህዝብ ላይ የማነሳሳት ከባድ ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ ራሳቸው የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፤ ‹‹ባለፉት ሁለት ዓመታት በበርካታ ሚዲያዎች የተፈጸመው ህገ ወጥ ተግባር ፈቃድ ሊያስነጥቅ የሚችል ነበር›› ብለዋል፡፡ የዳሬክተሩን አስተያየት ተንተርሰው ሐሳብ የሰጡ የጉባዔው ተሳታፊዎችም ‹‹የባለስልጣኑ ተግባር ከኃላፊነት የሚያስነሳ ወይም ስልጣን የሚያስለቅቅ ነበር›› ሲሉ የአጸፋ አስተያየት ሰንዝረዋል፡፡ ይህን ሁሉ የሚሰማው የኢትዮጵያ ህዝብ ይታዘባል፡፡ የህግ ባለሙያዎች ‹‹አንተ የሰው ሐብት

ዘርፈሃል›› ሲባል ‹‹አንተስ አልዘረፍክም›› የሚል ምላሽ ከወንጀል ነጻ አያደርግም ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ሌቦች ናቸው፡፡

‹‹ዳኛ የለም እንጂ፣ ቢኖርማ ዳኛ›› እያልን የባልስልጣኑን እና የባለፈቃዶቹን ክርክር ሰማን፡፡ እውነቱን ለመናገር፣ ህዝብን በህዝብ ላይ ታነሳሳላችሁ›› እያለ የነጻውን ፕሬስ ሲከስስ እና ሲያስር በቆየው መንግስት ቁጥጥር ሥር የሚገኙ የመገናኛ ብዙሃን፣ ህዝብን በህዝብ ላይ የማነሳሳት ተግባር ውስጥ ተጠምደው አየናቸው፡፡ ‹‹ዳኛ የለም እንጂ፣ ቢኖርማ ዳኛ›› እነሱም ዘብጥያ ይርዱ ነበር፡፡ ‹‹እናከብረዋለን - እናስከብረዋለን›› የሚሉትን ህገ መንግስት ሲጥሱት እና ሲያዋርዱት ተመለከትን፡፡ የባለፈቃዶቹን አሰራር የመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት የብሮድካስት ባለስልጣንም ‹‹እርምጃ ያልወሰድኩት ነገሩን ላለማባባስ ብዬ ነው›› አለን፡፡ በዝምታ ወይም ባለማድረግ ህገ መንግስቱን ሲጥስ የከረመው ብሮድካስት (አሁን ያደረገውን ጉባዔ እንኳን ማድረግ ተስኖት) የችግሩ አባሪ -ተባባሪ ሆኖ ቆይቶ፣ ‹‹የደቡብ ቴሌቭዥን የተፈጠረውን ትርምስ በዝምታ ይመለከት ነበር›› ብሎ ሲወቅስ ሰማን፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከገዢው ፓርቲ እና ከመንግስት ይልቅ የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ከመንግስት ሚዲያዎች ይልቅ የግል ፕሬሶች እና የንግድ ብሮድካስተሮች ሐገርን ከጥፋት ለመጠበቅ የሚያስችል የተሻለ ሥራ የሰሩ ይመስለኛል፡፡ በዚህ በኩል ያለውን ጉድ እዚህ ትተን፣ በብሮድካስት አገልግሎት ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ ችግሮችን በማንሳት ስለወደፊቱ ሁኔታ እንነጋገር፡፡

የብሮድካስት ባለስልጣን በውጭ ሐገር ተመዝግበው በኢትዮጵያ የቴሌቭዥን ስርጭት የሚካሄዱ ጣቢያዎችን እንዴት እንደሚያስተናግዳቸው የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ አሁን ባለው የቴክኖሎጂ ሁኔታ የብሮድካስት ባለስልጣን ለመቆጣጠር ቢፈልግም፣ ለቁጥጥር አስቸጋሪ የሚሆኑ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ለማስፈጸም የማይቻል ድንጋጌ አውጥቶ፣ በድሮ በሬ ለማረስ ከመሞከር ይልቅ፣ የኢትዮጵያ የብሮድካስት አገልግሎት ለመቆጣጠር የሚችለውን ነገር በደንብ ለይቶ አውቆ ‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ ውሱን የጋራ ሐብት›› የሚለውን የአየር ሞገድ በተሻለ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚችልበትን ሁኔታ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

አሁን ባለው ቴክኖሎጂ የአየር ሞገድ ውስን ሐብት መሆኑ የቀረ ይመስለኛል፡፡ የአንዱ ጣቢያ ስርጭት ከሌላው ጋር ግጭት ሳይፈጠር በጣም ተቀራራቢ በሆኑ የአየር ሞገዶች ስርጭት ለማድረግ የሚቻልበት ቴክኖሎጂ እውን ሆኗል፡፡ በመሆኑም፣ የአየር ሞገድ ውስን ሐብት መሆኑን በመጥቀስ፣ አጠቃቀሙን ለመቆጣጠር የወጣው ህግ ከንቱ ይመስለኛል፡፡ አንድም፣ ሐብቱ ውስን ስላልሆነ፣ አንድም ለቁጥጥር አስቸጋሪ ስለሆነ፡፡

ለምሣሌ፤ በሐገራችን ህግ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሐይማኖት ድርጅቶች የብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ፈቃድ አይሰጣቸውም፡፡ ሆኖም በርካታ የሐይማኖት ድርጅቶች የቴሌቭዥን ሥርጭት ሲካሄዱ እንመለከታለን፡፡ የብሮድካስት ባለስልጣን እነዚህን ተቋማት በዝምታ እያያቸው ነው፡፡ ይህን ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚችልም አይመስለኝም፡፡ በአጠቃላይ በሰሞኑ ውይይት የብሮድካሰት ባለስልጣን ምን ያህል ደካማ ተቋም መሆኑን ብቻ ሳይሆን፤ የሚሰራውን የሚያውቅ መሆኑን ለመጠራጠር የሚያበቃ ሁኔታ ተመልክተናል፡፡ ሌላው ቀርቶ የሞኒተሪንግ ሥራ ለመስራት የማይችል ተቋም መሆኑን አይተናል፡፡

በአንጻሩ፤ የሐገራችን የመንግስት ሚዲያዎችም ከምን ደረጃ ሊወርዱ እንደሚችሉ አይተናል፡፡ የኢትዮጵያ ሚዲያዎች ሐገርን ሊያፈርስ የሚችል ሥራ ለመስራት የሚችሉ መሆናቸውን ታዝበናል፡፡ ሐገሪቱ በህዝብ ጨዋነት እና ብቃት እንደ ሩዋንዳ፣ ሰርቢያ እና ዩጎዝላቪያ ያለ ሁኔታ ባይከሰትም፤ የእኛ ሚዲያዎች በተጠቀሱት ሐገራት የነበሩ ሚዲያዎች ሲሰሩ የነበሩትን ነገር ሲሰሩ አይተናል፡፡ የእኛ ባለስልጣናት፤ በሩዋንዳ፣ ሰርቢያ እና ዩጎዝላቪያ የሐገር ሞት ሲጎትቱ የነበሩ የተለያዩ ቡድኖች፣ የጦር አበጋዞች ወይም የህዝብ አስተዳዳሪዎች ያደርጉት የነበረውን ነገር ሲያደርጉም ተመልክተናል፡፡ ‹‹ዳኛ የለም እንጂ፤ ቢኖርማ ዳኛ›› አሰኝተውናል፡፡ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችም ጸረ ህዝብ የመሆን ችሎታ እንዳላቸው አይተናል፡፡ ገዢው ፓርቲም ባለፉት አርባ ዓመታት ታሪኩ ታይቶ ከማይታወቅ የዝቅጠት ደረጃ መውረዱን ታዝበናል፡፡

በአጠቃላይ በመንግስት ሚዲያዎች የታየው ችግር፤ በገዢው ፓርቲ ውስጥ የታየው የአመራር ቀውስ መገለጫ መሆኑን ደጋግመን አስምረን፤ በዚሁ መስመር የመንግስት የሚዲያ ተቋማት ወይም ባለሙያዎች ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቁመት የሚልቅ ተክለ ሰውነት እንደ ሌላቸው መናገር ይኖርብናል፡፡ ሐገሪቱን ከተለያዩ አደጋዎች የመጠበቅ እና በመርህ ላይ የተመሠረተ አመራር የመስጠት ኃላፊነት የተጣለባቸው የመንግስት ተቋማትም፤ ለክፉ ቀን የሚሆን የሞራል ፀጋ እንደሌላቸው ታዝበናል፡፡

እንዲሁም፤ ኢህአዴግ የሚከተለው የብሔር፣ ብሔረሰብ እና ህዝብ መብትን የማስከበር የፖለቲካ መርህ፤ ሁኔታዎች ሲበላሹ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል በቅርብ ርቀት ተመልክተናል፡፡ የብሔር፣ ብሔረሰብ እና ህዝብ መብትን ለማስከበር የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ እንወክለዋለን የሚሉትን የቡድን መብት ለማስከበር የሚያደርጉት ጥረት ሊሳካ የሚችለው የሁሉንም የሐገሪቱን ህዝቦች ጥቅም የሚያስከብር መርህ በመከተል መሆኑን መረዳት ሲቸግራቸው አስተውለናል፡፡

በዚህ ረገድ አንድ ሊነሳ የሚገባው ነገር ይታየናል፡፡ ምናልባት ለብሔር፣ ብሔረሰቦች መብት በመታገል የምናውቃቸው ድርጅቶች አንጋፋ አመራሮች አሁን በመተካካት ከመጡት አዳዲስ አመራሮች የሚሻሉበት አንድ ነገር ይታየኛል፡፡ ነባሮቹ አመራሮች የርዕተ ዓለም መሠረታቸው ሶሻሊዝም ወይም ኮምዩኒዝም ነበር፡፡ በመሆኑም፤ የአንድ ብሔርን መብት ለማስከበር የሚያደርጉትን ጥረት ከመደባዊ ጥያቄዎች ጋር አገናዝቦ የመመልከት ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ ቀዳሚዎቹ ታጋዮች ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን የሚያስቡ አመራሮች እና ታጋዮች ነበሩ፡፡ የአንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ አባል በሆኑ የተለያየ ባህል እና ቋንቋ ባላቸው ህዝቦች መካከል ልዩነት ብቻ ሳይሆን አንድነትም ይታያቸዋል፡፡ በዓለም ወዛደሮች መካከል የትግል አጋርነት መኖሩን የሚያምኑ፤ የትግላቸው የመጨረሻ ግብ ወደዚህ ምዕራፍ መድረስ መሆኑን ተቀብለው ለብድን መብት የሚታገሉ በመሆናቸው፤ ርዕዮተ ዓለማዊ ዝግጅታቸው ከቋንቋ እና ከባህል ባሻገር ያለውን የህዝቦች ግንኙነት ለማየት የሚያስችላቸው ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

አሁን ያሉት አመራሮች በዚህ ረገድ ሰፊ ክፍተት ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ አዲሱ ተተኪ አመራር ፈረንጆች ‹‹ፕራይሞርዲያል›› በሚሉት ነገር የታጀለ አመለካከት የያዙ መስለው ታይተውኛል፡፡ ማርክሲስቶች ‹‹ሐሳዊ ንቃተ ህሊና›› (false conciousness) በሚሉት ችግር ተጠልፈዋል፡፡ ከብሔር መብት ከፍ የሚል ርዕዮተ ዓለማዊ መነጽር ያላቸው አይመስሉኝም፡፡ ስለዚህ ሁኔታዎች ሲያጋድሉ በቀላሉ ይወድቃሉ፡፡ ድርጅቱ ‹‹ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት›› የሚለው አስተሳሰብ አይጠብቃቸውም፡፡ ድርጅቱ ‹‹ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት›› የሚለው ከብሔር አጥር ሊሻገር የሚችል እሳቤ ነው፡፡ ይህ እሳቤ ‹‹የጭቁኑን ህዝብ ጥቅምን ከሚጻረር የኦሮሞ፣ የትግራይ፣ የወላይታ ወይም ወዘተ አማራ ተወላጅ ይልቅ፤ የጭቁኑን የአማራ፣ የትግራይ፣ የኦሮሞ ወይም የወላይታ ወዘተ ህዝብን ጥቅም ለማስከበር የሚቆም በብሔር የተለየ ኃይልን አጋር አድርጎ መመልከትን›› የሚያቀነቅን አስተሳሰብ ነው፡፡

አሁን የምንመለከተው ሁኔታ ከዚህ መርህ የወጣ አካሄድ ነው፡፡ እናም የኢትዮጵያ ህዝብ ከፖለቲካ መሪዎቹ የላቀ አስተሳሰብ ያለው አስተዋይ ህዝብ በመሆኑ ለጊዜው ከአንዣበበው አደጋ ተጠብቀናል፡፡ የሐገራችን የህዝብ ሚዲያዎችም ‹‹ተነስ ወገንህ እያለቀ ነው›› ብለው ሲቀሰቅሱ ዝም ብሎ የማለፍ ህሊና መያዝ ችለዋል፡፡ ራሳቸውን የስርዓቱ ባለቤት እና ጠበቃ አድርገው ከሚመለከቱ የገዢው ፓርቲ የፖለቲካ አመራሮች ይልቅ፤ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የህዝቡ ሰላም እንዳይረበሽ ከወትሮ የተለየ ጥንቃቄ ሲያደርጉ አይተናል፡፡ ይህ ስርዓት ‹‹ከጠላቶቹ›› ብቻ ሳይሆን ‹‹ወዳጆቹ›› ጥቃት ሊሰነዘርበት እንደሚችል መረዳት ችለናል፡፡